**አዲስ ኪዳን የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን መተዳደሪያ ደንብ**

**አንቀጽ ፩**

ስም-የቤተ ክርስቲያኒቷ መታወቂያ ወይም ስም አዲስ ኪዳን የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን » ይሆናል።

**አንቀጽ ፪**

**አንቀጽ ፪ ክፍል ፩**

**ዋና ፅሕፈት ቤት**

በአሁኑ ወቅት የቤተ ክርስቲያኒቷ ዋና ጽ/ቤት ወይም መሥሪያ ቤት ሜሪላንድ ከተማ ውስጥ ይሆናል።

የቤተ ክርስቲያኒቱ ጽ/ቤት አድራሻ በሽማግሌዎች ጉባኤ ስምምነት በማናቸውም ወቅት ሊለወጥ ይችላል። የቤተ ክርስቲያኒቷን አድራሻ ለውጥ ደንቡን ላፀደቀው በሚመለከት የሚደረገው ማንኛውም የመንግሥት ክፍል ይጠቁማል፣ በአንፃሩም የተደረገው ለውጥ በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ ውስጥ በተገቢው ሥፍራ ይጠቀሳል።

**አንቀጽ ፪ ክፍል ፪**

የቤተ ክርስቲያኒቱ ዘርፍ ጽሕፈት ቤቶች

በማናቸውም ወቅት አቅም በፈቀደ መጠን የቤተክርስቲያኒቷ የሽማግሌዎች ጉባኤ ለማህበሩ ጽ/ቤት አጋዥ የሆኑ ንዑሳን ክፍሎችን (ጽህፈት ቤቶች) ሊያቋቁም ይችላል።

**አንቀጽ ፫ ተግባርና ዓላማ**

**አንቀጽ ፫ ክፍል ፩**

**ተግባር**

የቤተክርስቲያኒቱ አብይ ተግባር ቤተ ክርስቲያን ማቋቋም ይሆናል። ወንድም ሆነ ሴት ሳይቀር ሰው ሁሉ ኢየሱስ ክርስቶስን የግል አዳኝና ጌታ አድርጎ በመቀበል ዘላለማዊ ሕይወት በምልዐት እንዲያገኝና የክርስቲያኖች እምነትና ታማኝነት እንዲጠነክር ማድረግ መሠረታዊ ተግባሯ ይሆናል። በተጨማሪ ሜሪላንድ ከተማና በአካባቢው የክርስቲያን ታማኝነት እያደር እንዲጨምር፣ ቤተ ክርስቲያኖች እንዲያድጉና የተቸገሩ የሚረዱባቸው የበጎ አድራጎት ሥራዎች እንዲስፋፉ ማድረግ ተግባሯ ይሆናል።

**አንቀጽ ፫ ክፍል ፪**

**ዓላማ**

**የቤተ ክርስቲያኒቱ መሠረታዊ ዓላማ**

**አንቀጽ ፫ ክፍል ፪-፩**

**አዲስ ኪዳን የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ማካሄድ፣**

**አንቀጽ ፫ ክፍል ፪፪**

ለዚህ ዓላማ የሚረዱ የተለያዩ ስጦታዎች፣ ንብረቶች፣ ኑዛዜዎች፣ ሌሎች ገጸ በረከቶችና እርዳታዎችን መቀበል።

**አንቀጽ ፫ ክፍል ፪-፫**

ለእዚህ ተግባሮች ቅልጣፌ አስፈላጊ የሆኑ ምቹ መሬቶችን፣ ህንፃዎችንና ሌሎችንም የግል ንብረቶች መያዝ መንከባከብና ማከራየት፣ እንዲሁም ለቤተክርስቲያኒቱ ዓላማ ክንዋኔ ምቹነት የገቢ ምንጭ ሊያስገኙ በሚችሉ በማናቸውም ሕጋዊ የሥራ ዘርፎች (ኮንትራት) ያለገደብ መሳተፍ ይሆናል።

**አንቀጽ ፬**

**አንቀጽ ፬ ክፍል ፩**

**ገለልተኛ (ፖለቲካ-አልባ) እንቅስቃሴዎች**

ይህች ቤተክርስቲያን ከላይ እንደተዘረዘረው ለሃይማኖት ተግባር ብቻ እንድትውል በሜሪላንድ መንግሥት የማህበር ህግ መወሠረት የተቋቋመች ስለሆነች ትርፍ አልባና ኢፖለቲካዊ (ፖለቲካዊ ያልሆነች) ትሆናለች። ይህች ቤተክርስቲያን በምንም

ዓይነት መንገድ የአገሪቱን ህግና የፖለቲካ ይዘት የሚተች ወይም ሊያዛባ የሚችል ጽሑፍ አታሰራጭም።

- ይህች ቤተ ክርስቲያን በማንኛውም ዓይነት መንገድ ለመመረጥ ወይም ለመምረጥ የፖለቲካ ዘመቻ ለሚያደርጉ ግለሰቦች ድጋፍ አትሰጥም፣ ጣልቃ-ገብ ተሳትፎም አታደርግም።
- ቤተ - ክርስቲያኒቱ ከላይ የተጠቀሱትንና መሰል የፖለቲካ ሁኔታዎችን አታስተናግድም።

**አንቀጽ ፬ ክፍል ፪**

**ተልኮን ከግብ ማድረሻ መንገዶች**

ይህች ቤተክርስቲያን (ተልኮዋን) ዓላማዋን በተግባር የምትተረጉመው የሚከተሉትን ዘዴዎች (መንገዶች) በመጠቀም ይሆናል።

**<u>፬.፪-፩</u>**

የእግዚአብሔርን ቃል መስበክና ማስተማር

**<u>፬. ፪-፪</u>**

ማምለክ፣ መጸለይ፣ መምከርና የተሃድሶ ስብሰባዎችን ማካሄድ

**<u>፬. ፪-፫</u>**

ጥናት የሚረዱ ጽሁፎችን፣ ቴፖችን፣ወንጌላዊ ጽሁፎችን፣ መጽሔቶችን፣ መዝሙሮችን፣ ለመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚረዱ ጽሁፎች ወዘተ ማስፋፋትና ማሰራጨት።

**<u>፬. ፪-፬</u>**

መንፈሳዊ ይዘት ያላቸው ማህበራዊ እንቅስቃሴዎችን ማስፋፋት

**<u>፬. ፪-፭</u>**

የግላዊና የህብረት የወንጌል ሥርጭት ማካሄድ

**አንቀጽ ፭**

የእምነት መግለጫ

**አንቀጽ ፭ ክፍል ፩**

መጽሐፍ ቅዱስ

መጽሐፍ ቅዱስ ማለትም ብሉይና አዲስ ኪዳን በምልዐት በእግዚአብሔር መንፈስ መሪነት የተጻፈ የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን እናምናለን፣

እንዲሁም እንከን አልባ የሆነና በሰውም እምነትና ሕይወት ላይ የመጨረሻ ከፍተኛ ሥልጣን ያለውና የቤተ ክርስቲያን እምነትና ሥርዓት መሠረት መጽሐፍ ቅዱስ መሆኑን እናምናለን፣ 2ኛ ቆሮ.1፥21፣ 2ኛ ጢሞ.3፥16፣ ሮሜ 15፥16፣ 1ኛ ቆሮ.10፥11።

**አንቀጽ ፭ ክፍል ፪**

እግዚአብሔር ለዘለዓለም ፀንቶ በሚኖርና ራሱን በሦስት አካል በአብ፣ በወልድ፣ በመንፈስ ቅዱስ በሚገልጥበት በአንድ አምላክ እናምናለን፣ ማቴ.28፥19-20 እና 2ኛቆሮ.13፥14

**<u>፭-፪-፩</u>**

ሃያልና ዘለዓለማዊ በሆነ የሚታየውንና የማይታየውን ሁሉ በፈጠረ በእግዚአብሔር አብ እናምናለን፣ ዘፍ.1፥1–2፣ 7 1ኛ ቆሮ.8፥6 2ኛ ቆሮ.6፥18 እና 1ኛ ጢሞ.1፥17

**<u>፭-፪-፪</u>**

ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን፣ ከድንግል ማርያም መወለዱን፣ ፍጹም አምላክና ፍጹም ሰው መሆኑን፣ ስለ ሐጢአታችን በመስቀል ላይ የተሰ ቃየ፣ የሞተና የተቀበረ እንዲሁም በሦስተኛው ቀን ከሞት በአካል ተነስቶ ለሰዎች የተገለጠና በክብር

ወደ ሰማይ ያረገ መሆኑን፣ አሁንም በአባቱ ቀኝ ተቀምጦ ዘወትር ለእኛ እንደሚማልድና፣ ዳግመኛ በታላቅ ክብርና ሥልጣን እንደሚመለስ እናምናለን፣ ማቴ.16፥16 ዮሐ.5፥20 ማቴ.1፥23 1ቆሮ.15፥3- 7 የሐዋ.1፥9–11 እና ማቴ.24፥30

**፭–፪-፫**

መንፈስ ቅዱስ (አጽናኙ) መንፈሳዊ አባቶችን፣ ነብያት ንና ሃዋርያትን እንዳንቀሳቀሰና እንደመራ እንዲሁም ባሁኑ ዘመን በአማኞች ውስጥ አድሮ መንፈሳዊ ስጦታዎችንና ሃይልን በማከፋፈል ቤተ ክርስቲያንን እንደሚቀድስና ዓለምንም ስለ ሃጢያት፣ ስለጽድቅና ስለፍርድ እንደሚወቅስ እናምናለን፣ ዮሐ.14፥26 2ኛ ጴጥ.1፥21 የሐዋ.1፥8 1ኛ ቆሮ.12፥4–11 ኤፌ.4፥11-12 እና ዮሐ 16፥18

**አንቀጽ ፭ ክፍል ፫**

ዳግም ልደት (ደህንነት)

ሰው ያለ ኃጢያት መፈጠሩን እናምናለን፣ ይሁን እንጂ በፈቃደኝነት ሃጥያት ላይ ስለወደቀ ሰበዋ ፍጡር ሁሉ የሚወለደው የሃጥያት በህርይ ይዞ እንደሆነ፣እንዲሁም በሃጥያቱ ተጸጽቶና ንስሃ ገብቶ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኙ ና ጌታውን የተቀበለ ሁሉ ከመንፈስ ቅዱስ እንደተወለደና የእግዚአብሔር ልጅም እንደሆነ እናምናለን፣ዘፍ.3፥1-24 ሮሜ.5፥12-19 ሮሜ.6፥23-24 ሮሜ.10፥9-19 ዮሐ.1፥12-13 ሮሜ.3፥1-16

**አንቀጽ ፭ ክፍል ፬**

የውሃ ጥምቀት

የውሃ ጥምቀት ሥርዓት መከናወን ያለበት ስለ ሃጢያታቸው ንሰሃ ገብተው ኢየሱስ ክርስቶስን የግል አዳኝና ጌታ በማድረግ በልባቸውም በእውነት ለተቀበሉ ሁሉ መሆኑንና ይህም ፣ ሥርዓት ምዕመናን ከክርስቶስ ጋር መሞታቸውን፣ መነሳታቸውንና ከእርሱም ጋር በአዲስ ሕይወት መራመዳቸውን ለዓለም የሚያበስሩበት መሆኑን እናምናለን።

**አንቀጽ ፭ ክፍል ፭**

ቅዱስ ቁርባን (የጌታ ዕራት)

ከሕብስትና ከወይን ጭማቂ የሚዘጋጀው ቅዱስ ቁርባን የጌታችንና የመድኒታችን መለኮታ ባህርይ ተገንዝበን፣ የእርሱ ስቓይ፣ ሞትና እንደገና መመለስ የሚያሰስበን ተካፋይ መሆናችንን የሚያሳይ እንደሆነና እርሱ እስኪመጣ ድረስ በአማኞች መደረግ ያለበት ሥርዓት መሆኑን እናምናለን፣ 2ኛ.ጴጥ.1፥4 1ኛ.ቆሮ.11፥23- 26

**አንቀጽ ፭ ክፍል ፮**

ቅድስና

የክርስቲያኖች ጥሪ የእግዚአብሔርን ቃል እየታዘዙ የቅድስና ሕይወት መኖር፣ መንፈሳዊ ፍሬ ማፍራትና ኢየሱስ ክርስቶስን ከፍ ማድረግ እንደሆነ እናምናለን፣ ያዕ.1፥22-25 ሉቃ.8፥15 2ኛ ጢሞ.2፥19 ዕብ.12፥14 1ኛ ጴጥ.1፥5-16 ገላ.5፥22-24 1ኛ ዮሐ.2፥6

**አንቀጽ ፭ ክፍል ፯**

የክርስቶስ ዳግም ምጽአት

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መንግሥቱን ሊመሠርት እንደገና እንዲመጣ እናምናለን። እርሱ ሙታንን ያስነሳል፣

ለዘለዓለም በሚኖሩትና በሚሞቱት ላይ ፍርድ ይሰጣል፣ሃጢያተኖችን ከእግዚአብሔር ፊት ያስወግዳል፣ ጻድቃን ግን ከእርሱ ጋር ለዘለዓለም ይኖራሉ፣ ራዕ.20፥1-7 19፥11-14 ዮሐ.3፥16 ማቴ.25፥31-46 ራዕ.20፥10-15

**አንቀጽ ፮**

**አንቀጽ ፮ ክፍል ፩**

ትብብር (የሥራ ግንኙነት)

ይህች ቤተ ክርስቲያን የሜኖናይት ቤተ ክርስቲያን የወንጌል ተልዕኮና የበጎ አድራጎት ጉባኤ አባል ናት። ከዚህ ከተጠቀሰው መንፈሳዊ ድርጅት በስተቀር በዚች ቤተ ክርስቲያን ተግባርና ላፊነት፣ እንዲሁም ዓላማና የሥራ ግንኙነት ውስጥ ማናቸውም ሌላ ድርጅት ወይም ማህበረሰብ ጣልቃ መግባት አይችልም። ስለዚህ ቤተ ክርስቲያኒቷ ወንጌልን የሚያስፋፉ ጽሁፎች፣ ቴፖች፣ መጽሐፍቶች ወዘተ. ብቻ እንጂ የሌላ ድርጅት ዓላማ የሚያንፀባርቅ ጽሁፍ አታሰራጭም፣ እንዲሁም ሌላ ድርጅት ከቤተ ክርስቲያኒቱ ፈቃድ ውጭ በሆነ መንገድ ማናቸውም ዓይነት ጽሁፍ ለማሰራጨት ቤተ ክርስቲያኒቷን አይጠቀምም።

**አንቀጽ ፮ ክፍል ፪**

የንብረትና የሐብት ግልጋሎት

የዚህ ትርፍ አልባ ድርጅት ንብረትና ሐብት በማያወላውል ሁኔታ ለሃይማኖት ጉዳይ ብቻ ይውላል።ንብረቱና ሐብቱ ወይም ማናቸውም ዓይነት ተቀማጭምሆነ ተንቀሳቃሽ ሐብት ለግለሰቦች፣ ለቤተ-ክርስቲያን አባሎችና፣ ለቤተ-ክርስቲያን ሽማግሌዎች የግል ጥቅም አይውልም። ድርጅቱ ሲፈርስ ንብረቱና ሐብቱ በወቅቱ የተገኘውን እዳ ከከፈለ በኋላ ቀሪው ንብረት በአገር ውስጥ ገቢ መሥሪያ ቤት ሕግ አንቀጽ 501/ሲ/3/ መሠረት በተመሳሳይ ተግባር ላይ ለተሰማሩ ድርጅቶች ይከፍላል።

**ሽማግሌዎች**

**አንቀጽ ፯ ክፍል ፩**

ሥልጣን

መተዳደሪያ ደንብ

ሀ.የቤተ ክርስቲያኒቱ አጠቃላይ ሥልጣን

የሜሪላንድ መንግሥት ትርፍ አልባ ለሆኑ ድርጅቶች ያወጣው ሕግ፣ አንጻራዊ የሆኑ አንቀጾችና ደንቦች በሚያዙት መሠረት ቤተ ክርስቲያኒቱን የሚመለከት ጉዳይና ተግባር ሁሉ በሽማግሌዎች ጉባኤ ወይም ጉባኤው ባስተላለፈው መመሪያና ትዕዛዝ መሠረት ይከናወናል።

ለ. ዝርዝር ሥልጣኖች

የአጠቃላዩን የሥልጣን ገደብ ፈር ሳይለቅ የሽማግሌዎች ጉባኤ የሚከተሉት ሥልጣኖች ይኖሩታል።

ለ.፩-የሜሪላንድ መንግሥት ለትርፍ አልባ ድርጅቶች ያወጣውን ሕግ፣ አንፃራዊ አንቀጾችና ይህንን ደንብ ሳይጥስ የጉባኤውን የድምፅ ብልጫ ውሳኔ መሠረት በማድረግ ሠራተኞችን ይቀጥራል፣ የሥራ ሃላፊነትና ተግባር ይወስናል፣ እንዲሁም ለዚህ የሐላፊነት ደረጃ የሚገባውን ክፍያ ይመድባል።

ለ.፪-ከሜሪላንድ ከተማና ከአካባቢው ሳይወጣ ቤተ ክርስቲያኒቱን ከቦታ ቦታ መለዋወጥ ይችላል። ቤተ ክርስቲያኒቱ በየትኛውም አገር፣ ክፍለ፤ ተባባሪ ግዛትና በሌላም አገር የገቢ ምንጭ ሊያስገኝ የሚያስችል ሥራ (Business) የሚከናወንበትን መንገድና ዘዴ ያጠናል፣ በተግባርም ይተረጉማል።

እንደ አመቺነቱ በሲልቨር ስፕሪንግ ከተማና በአካባቢው እንዲሁም በሌሎች ሥፍራዎች በጉባኤው ድምፅ ብልጫ መሠረት ማንኛውም ዓይነት ስብሰባ ማካሄድ

ይችላል፣ ይህም ወርሃዊና ዓመታዊ ስብሰባዎችን ያጠቃልላል።

ለ.፫-የቤተ ክርስቲያኒቱን ማህተም ቅርጽና ይዘት መለወጥና ማሻሻል ይችላል።

ለ፬-በቤተ ክርስቲያኒቱ ስም ገንዘብ መበደርና ማበደር ይችላል፣ እንዲሁም የተሰበሰበው ገንዘብ ለቤተ ክርስቲያኒ ተግባር መዋሉን ያረጋግጣል፣ በቤተክርስቲያኒቱ ስም ስለት፣ ውርስ፣ ወለድ አገድ፣ በንድ የመሳሰሉትን ገቢዎች ይሰበስባል።

**አንቀጽ ፰**

**አንቀጽ ፰ ክፍል ፩**

የቤተ ክርስቲያን ጽህፈት ቤት ሹሞች

መጋቢው፣ ፀሐፊው፣ ሒሳብ ሹሙና የተቀሩት ሽማግሌዎች የቤተ ክርስቲያኒቱ ጽ/ቤት ሹሞች ይሆናሉ። አንድ ሹም ከአንድ በላይ ሥልጣን ሊኖረው ይችላል፣ ፀሐፊውና የሂሳብ ሹሙ ግን የመጋቢነት አገልግሎትን ደርበው ሊይዙ ወይም የሽማግሌዎች ጉባኤ ሊቀ መንበር ሊሆኑ አይችሉም።

**አንቀጽ ፰ ክፍል ፪**

፪.ሀ መጋቢ

- መጋቢው የቤተ ክርስቲያኒቱ መሪና የሽማግሌዎች ጉባዔ ሊቀመንበር ይሆናል። ቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ የተቋቋሙ ኮሚቴዎችን ሁሉ በሊቀመንበርነት ይመራል። ረዳት ፀሐፊ፣ ረዳት የሒሳብ ሹምና ሌሎች ሠራተኞችንም ይጠቁማል፣ ይመረጣል።
- የተመረጡትንና የተጠቆሙትን እጩ ሠራተኞች የስም ዝርዝር ለሽማግሌዎች ጉባዔ በማቅረብ በድምፅ ብልጫ እንዲፀድቅ ያደርጋል።
- የሜሪላንድ መንግሥት ትርፍ አልባ ለሆኑ ድርጅቶች ያወጣውን ሕግ፤ ተመሳሳይ ተግባሮችን ያከናውናል፣ የሽማግሌዎች ጉባዔ ያስተላለፈውን ውሳኔ በተግባር ላይ ያውላል።
- የእግዚአብሔር ቃል በሚያዘው መሠረት አዳዲስ የሽማግሌዎች ጉባዔ አባላት ጥቆማ በመጋቢው የሽማግሌዎች ጉባኤ ይደረጋል፣ የሐዋ.፲፬፥፳፫ እና የሐዋ.፩፥፳ በምዕመናንና በወቅቱ የሽማግሌዎች ጉባዔ የማጣራት ተግባሩን እንዳበቃ ለምዕመናን አቅርቦ ምርጫ ይካሄዳል። የሚመረጡት ሽማግሌዎች ቁጥር ከሰባት መብለጥ ከሦስት ማነስ የለበትም። ፀሐፊውና የሒሳብ ሹሙ የሽማግሌዎች ጉባዔ አባላት ሲሆኑ የሚሾሙት በመጋቢው ይሆናል።

የብቃት መመዘኛ

1. መለኮታዊ ጥሪ ያለው መሆን አለበት፣ ኤፌ ፬፥፲፩ እና የሐዋ.፳ ፰

2. የመጋቢነት ብቃት ሊኖረው ይገባል፣ ፩ጢሞ.፫፥፩-፯ ፩ጴጥ.1፥፩-፬

3. በቤተክርስቲያኒቱ የእምነት መግለጫ የሚያምንና መተዳደሪያውን ደንብ የሚያከብር ሊሆን ይገባል።

የመጋቢው ላፊነትና ተግባር

ሀ. የቤተ ክርስቲያኒቱን ምዕመናን በሙሉ፣ እንዲሁም ሽማግሌዎችንና በሥሩ የሚገኙትን ሌሎች መጋቢዎች ወይም ሙሉ ጊዜአቸውን የሰጡ አገልጋዮችንና በተለያዩ የአገልግሎት ዘርፎች የተሰማሩት መሪዎችን ሁሉ በቤተክርስቲያኒቱና በእግዚአብሔር ፊት ላፊነታቸውን የሚወጡበትን መንገድ ማስተማርና መምራት።

ለ.በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚካሄዱ እንቅስቃሴዎችን ማለትም አምልኮን፣ የተለያዩ

ትምህርቶችን፣ ልዩ ልዩ አገልግሎቶችንና ሌሎችንም ቤተ ክርስቲያኒቱ የምታድግባቸውን ዘዴዎች ያጠናል፣ ያቅዳል፣ እንዲሁም በሥራ መተርጎማቸውን ይቆጣጠራል፣ የቤተ ክርስቲያንኒቱን አባላት ቤተሰቦች መንፈሳዊ ዕድገት ይገመግማል።

ሐ- ምዕመናንን ይጎበኛል፣ ምክሩንም ለሚሹ ምክር ይለግሳል።

መ. በተጠየቀበት ወቅት ሁሉ በሥፍራው በመገኘትም ሆነ የተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም ሕብረሰባዊ ለሆኑ ጉዳዮች መንፈሳዊ አገልግሎት ይሰጣል።

የአገልግሎት ዘመን ርዝመት

የመጋቢው የአገልግሎት ዘመን የጊዜ ገደብ የለውም።

ከአገልግሎት መወገድ

1. መጋቢው ከአገልግሎት ከመወገዱ ከሦስት ወር (90 ቀናት) በፊት ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል። ይህ የጊዜ ገደብ በጉባዔው ስምምነት ሊለወጥ ይችላል።

2.መጋቢውን ከአገልግሎት ለማስወገድ የሚወሰዱ እርምጃዎች፡-

ሀ.በአንቀጽ ፲. በክፍል ፩ በቁጥር ፪ መሠረት ጉባዔ ይጠራል

ለ.ከሁለት ሳምንት በፊት ለምዕመኑ ከተነገረና የሽማግሌዎችም ጉባዔ በቁጥር ፩ ላይ የተጠቀሰውን እርምጃ ከወሰደ በኋላ ጉዳዩ በመደበኛ የሽማግሌዎች ጉባዔ አጀንዳ ውስጥ ተይዞ ለውይይት ይቀርባል።

ሐ የሽማግሌዎች ጉባዔ የደረሰበትን ውሳኔ ሁለት ሦስተኛውን እጅ ምዕመን ከደገፈው መጋቢው ከአገልግሎቱ ይወገዳል።

መ.መጋቢው የቤተ ክርስቲያኒቱን ሕግ ሲተላለፍ ወይም የሞራል ውድቀት ወይም ግድፈት ሲገኝበት ወዲያውኑ ከሥራ ይገለልና በሰላሳ ቀናት ውስጥ የሽማግሌዎች ጉባዔ ጉዳዩን ለምዕመናን ጉባዔ አቅርቦ በድምፅ ብልጫ ይወሰንበታል።

የመጋቢ ሹመትና ቅድመ ዝግጅት

1.መጋቢ በሌለበት ወቅት የቤተክርስቲያኒቱን አምልኮና የሃይማኖት ትምህርት መርሃ ግብር የሚያሰናዱና የሚያቀናብሩ ኮሚቴዎችን የሽማግሌዎች ጉባዔ ይሾማል።በዚህ ወቅት የሽማግሌዎችን ጉባዔ በሊቀመንበርነት የሚመራው ግለሰብ የቤተ ክርስቲያኒቱ መሪ ሆኖ ያገለግላል።

2. የሽማግሌዎች ጉባዔ መለኮታዊ ጥሪ ያለውን ግለሰብ በጥንቃቄ መርጦ በመለየት ለምዕመን ጉባዔ ያቀርባል።

3.የሽማግሌዎች ጉባዔ ለምዕመናን የሚያቀርበው እጩ በቁጥር ከአንድ መብለጥ የለበትም። ይህ እጩ ግለሰብ ለምዕመኑ የሚቀርበው በሽማግሌዎች ጉባዔ ውስጥ በድምፅ ብልጫ ሲመረጥ ብቻ ነው።

4.የሽማግሌዎች ጉባዔ ይህንን በተመለከተ ከምዕመናኑ ጋር ለመነጋገር ቢያንስ ከሁለት ሳምንት በፊት የስብሰባ ጥሪ ያደርጋል።

5.የመጋቢው ሹመት የሚያጸድቀው የመምረጥ መብት ካላቸው ምዕመናን መካከል ሁለት ሦስተኛው ሲመርጠው ብቻ ነው።

**የፀሐፊው ሐላፊነትና ተግባር**

ፀሐፊ፡

ቃለ ጉባዔዎችን፣ ውሳኔዎችን፣ ትዕዛዞችንና በየጊዜውም በተለያዩ ኮሚቴዎች የሚተላለፉትን ውሳኔዎች በመጋቢው ጽ/ቤት ወይም በሌላ ለዚህ ተግባር በተዘጋጀ ቦታ የመዝገብ አያያዝ ስልትን በመጠቀም መልክ አስይዞ ያስቀምጣል።

**የሒሳብ ሹም ላፊነትና ተግባር፡**

ሀ. የሒሳብ ክፍል ሹሙ ቤተ ክርስቲያኒቱን የሚመለከቱ የሒሳብ ሥራዎችን ማለትም

- የሚንቀሳቀሱና የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን
- የወጪና የገቢ ሒሳብ ደረሰኞችን
- የድርጅቱን ካፒታልና
- ሌሎችንም ሒሳብ-ነክ ጉዳዮች የሒሳብ መዝገብ አያያዝ ስልትን በመከተል በጥንቃቄ ይይዛል። ይህ መዝገብ በየትኛውም ወቅትና በማናቸውም የሽማግሌዎችጉባኤ አባል ሊመረመር ይችላል።

ለ.ገንዘብ የማውጣትና ሂሳብ የመክፈል ደንብ

የሂሳብ ክፍል ሹም በሽማግሌዎች ጉባኤ ትእዛዝ፡-

- በቤተክርስቲያኒቱ ስም ገንዘብና የተለያዩ ንብረቶችን በተገቢው ቦታ እንዲቀመጥ ያደርጋል።
- የድርጅቱ ወጪዎች እንደ አስፈላጊነታቸው መሸፈናቸውን ያረጋግጣል።
- የሚያከናውናቸውን የቤተክርስቲያኒቱን ገንዘብ ነክ እንቅስቃሴዎችና የወቅቱን በቤተ ክስቲያኒቱን የገንዘብ ሁኔታ እንዲገልጽ በመጋቢ ወይም በሽማግሌዎች ሲጠየቅ በሙሉ ተባባሪነት የተጠየቀውን ያደርጋል።
- በሽማግሌዎች ጉባኤ የሚሰጡትን ሌሎች የስራ ሃላፊነቶች ያከናውናል።

**ሐ ዋስትና**

አስፈላጊ ከሆነ፣ የሒሳብ ሹም በመሆን እንዲያገለግል የሚታጨው ግለሰብ በሽማግሌዎች ጉባኤ ዋስ እንዲያቀርብ ቢጠይቅ በላፊነት የሚያንቀሳቅሰውን ገንዘብ፣ መዝገብ፣ ደረሰኞችና ሌሎች ዋጋ ሊያወጡ የሚችሉ ንበረቶችን መሸፈን የሚችል ብቁ ዋስ ያቀርባል።

**አንቀጽ ፱**

ሽማግሌዎች

የሽማግሌዎች ቁጥር፡-

የሽማግሌዎች ቁጥር ከሶስት እስከ ሰባት ይሆናል።

**አንቀጽ ፱ ክፍል ፩**

የሽማግሌዎች ብቃት መመዘኛ

**፱ – ፩ – ፩**

ሕይወታቸውን ለጌታ ኢየሱስ አሳልፈው የሰጡ

**፱ – ፩ –፪**

በእግዚአብሔርና በሰው ዘንድ በንጽህና የሚኖሩ

**፱-፩-፫**

በቤተ ክርስቲያኒቱ የእምነት መግለጫ የሚያምኑ

**፱-፩-፬**

የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን በቆመችለት ዓላማ የሚያምኑ

**፱–፩-፭**

ቀደም ሲል በክርስትና አገልግሎት ውስጥ ተሳትፎ የነበራቸው

**፱–፩-፮**

ሽማግሌዎች ጊዜያቸውን፣ ጉልበታቸውንና እግዚአብሔር የሰጣቸውን ጥበብ በእግዚአብሔር ሥራ ላይ ለማዋል ፈቃደኞች የሆኑና በተጨማሪም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በ፩ጢሞ.፫፥፩-፯ በቲቶ ፩፥፮-፱ የተገለጸውን ዝርዝር ሁኔታ የሚያሟሉ መሆን አለባቸው።

**አንቀጽ ፱ ክፍል ፪**

የሽማግሌዎች ኃላፊነትና ተግባር

**፱–፪– ፩**

የሽማግሌዎች ጉባዔ የመጋቢው አማካሪ፣ ረዳትና ባልደረባ ይሆናል።የሽማግሌዎች ጉባዔ ይህንን ድርሻውን በሚወጣበት ጊዜ መጋቢው ከእግዚአብሔር የተቀበለውን ራዕይ በሥራ እንዲተረጉም ይረዳዋል።

**፱–፪–፪**

ከመጋቢው በሚቀርቡለት ሀሳቦች፣ በአጀንዳ በተያዙ ጉዳዮችና በሌሎች አስቸኳይ ነገሮች ላይ ተነጋግሮ ለመወሰን የሽማግሌዎች ጉባዔ በወር አንዴ ይሰበሰባል።

**፱ – ፪ – ፫**

ሽማግሌዎች ጉባዔዎችን የሚያካሂዱትና ሌሎች ሥራቸውን የሚከናውኑት በመጋቢው ሊቀመንበርነት ነው።

**፱- ፪-፬**

ሽማግሌዎች በምክር መስጠት አገልግሎት ላይ ተሳታፊ በመሆን መጋቢውን ይረዱታል።

**፱- ፪-፭**

በምዕመናን መካከል ሁከት፣ ሕገ ወጥነት፣ የእምነት ጉድለትና የሞራል ውድቀት በሚደረስበት ወቅት መጋቢው ለሚወስደው የቅጣት እርምጃ ሽማግሌዎች ዕርዳታ ይሰጡታል።

**፱- ፪-፮**

መጋቢው በየምዕመናኑ ቤት እየተዘዋወረና ወደ ሆስፒታሎች እየሄደ በሚያደርጋቸው የጉብኝት ሥራዎች ሽማግሌዎች ተሳታፊ ይሆናሉ።

**፱-፪-፯**

መጋቢው ምዕመኑን በወንጌል ትምህርት ለማሳደግ በሚያደርገው ጥረት ሽማግሌዎች ይተባበራሉ።

**፱-፪-፰**

መጋቢው በሚያካሄደው የቁርባን ሥነሥርዓት ላይ ሽማግሌዎች ተሳትፎ ያደርጋሉ።

**፱–፪–፱**

ሽማግሌዎች በዚህ ደንብ በአንቀጽ ፰ ላይ የተዘረዘረውን ተግባር ያከናውናሉ።

**፱–፪–፲**

ሽማግሌዎች የመጋቢውን ደመወዝ፣ ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ አበሎቹንና የመጓጓዣ ወጪዎችን ይወስናሉ።

**፱–፪–፲፩**

ሽማግሌዎች አባል ለመሆን የሚጠይቁ ሰዎችን ማመልከቻዎች ይመዝናሉ፣ በአባልነትም ይቀበላሉ።

**አንቀጽ ፱ ክፍል ፫ ቅጣትና ከሹመት መወገድ**

ማንኛውም የሽማግሌዎች ጉባዔ አባል ሃላፊነቱን ቸል ቢል ወይም የዶክትሪን ጉድለት ቢገኝበት በሽማግሌዎች ጉባዔ ከሽማግሌዎች ጉባዔ አባልነት እንዲወገዱ ያደርጋል። ይህንን ውሳኔ ለማጽደቅ በ30 ቀናት ውስጥ ጠቅላላው ጉባዔ ለስብሰባ ይጠራል።

**አንቀጽ ፱ ክፍል ፬ ክፍት ሥፍራ**

በሽማግሌዎች ጉባዔ ውስጥ የሚገኝ ክፍት ሥፍራ ሲኖር የሚሸፈነው ወይም በሌላ አባል የሚተካው በልዩ ወይም ወርሃዊ የምዕመን ጉባዔ የምርጫ ውጤት ይሆናል።

**አንቀጽ ፱ ክፍል ፭ ሥልጣንን በፈቃድ መልቀቅ**

ማንኛውም የሽማግሌዎች ጉባዔ አባል በፈቃደኝነት ሥልጣኑን መልቀቅ ሲፈልግ ምክንያቱን በጽሑፍ

ለመጋቢው ያቀርብና ጉዳዩ በሽማግሌዎች ጉባዔ ተጠንቶ ሲያበቃ መብቱ ተጠብቆለት ስንብት ይደረግለታል።

**አንቀጽ ፱ ክፍል ፮ የአገልግሎት ዘመን ርዝመት**

የሽማግሌዎች ጉባዔ አባል የአገልግሎት ዘመን ሁለት ዓመት ይሆናል፣ ስለዚህ እያንዳንዱ የተመረጠ ሽማግሌ የሚያገለግለው ለሁለት ዓመት ይሆናል ማለት ነው። ማንኛውም ሽማግሌ ከሁለት የምርጫ ጊዜ ማለትም ከአራት ዓመት በላይ በተከታታይ ማገልገል አይችልም። አንድ የምርጫ ጊዜ (ሁለት ዓመት) ካሳለፈ ወይም ከዘለለ በላ ግን እንደገና መመረጥ ይችላል። በቂ ምትክ የማይገኝ ከሆነና የተቀሩት ሽማግሌዎች በእርሱ መቀጠል ከተሰማሙ ለሦስተኛ ጊዜ ተመርጦ ሊያገለግል ይችላል።

ያሉት ሽማግሌዎች እኩሌታ ለሁለተኛ የአገልግሎት ዘመን በቀጥታ ይቀጥላል። የተቀረው እኩሌታ ግን አዲስ በሚመረጡት ሽማግሌዎች ይተካል። የሚተኩና የሚቀጥሉት ሽማግሌዎች የሚለዩት በሚከተለው ሁኔታ ይሆናል።

ሀ. ሁለት ተከታታይ ያገልግሎት ዘመን ያገለገሉ ሽማግሌዎች የመጀመሪያ ተተኪዎች ይሆናሉ።

ለ. ሁለት ተከታታይ ያገልግሎት ዘመን ያገለገሉ ባይኖሩና ካሉት ሽማግሌዎች መካከል በግል ጉዳይ ለሁለተኛ ጊዜ መቀጠል የማይፈልጉ ቢኖሩ ምርጫው ከመደረጉ አንድ ወር አስቀድመው ያስታውቁና አዲስ በሚመረጡት ይተካሉ።

**አንቀጽ ፱ ክፍል ፯ የሽማግሌዎች አመራረጥ**

በአንቀጽ ፱ በክፍል ፩ መሠረት መጋቢው፣ ሽማግሌዎችና ምዕመኑና ብቁ የሆኑ ሰዎችን የመጠቆም እኩል ድርሻ (ሲሶ እጅ) ይኖራቸዋል።

የሽማግሌዎች ጉባዔ በአንቀጽ ፱ በክፍል ፩ መሠረት የተጠቆሙት ሰዎች የብቃት መመዘኛውን ማሟላታቸውን መመዘኛውን ካሟሉት መካከል ለምርጫ የሚቀርቡት ሰዎች ቁጥር ካለው ክፍት ቦታ በሁለት የበለጠ መሆን አለበት። ከሦስቱ ጠቋሚ ያመሰክራል። ክፍሎች ተመሳሳይ ጥቆማ ቢኖር ሽማግሌዎች ሌሎችን በመጠቆም የጎደለውን ቁጥር ይሞላሉ።

አባሎች ለሽምግልና የሚመርጧቸው ሰዎች ተጠቁመው ለምርጫ ካቀረቡአቸው ሰዎች መካከል ነው። ከፍተኛውን የአባላት የድምፅ ብልጫ ያገኙት ሰዎች በሽማግሌነት ያገለግላሉ።

**ክፍል ፰ የዲያቆናት ቅጣት፣**

ከአገልግሎት መወገድና ሥልጣንን በፈቃድ መልቀቅ

በአንቀጽ ፱ ሀ በክፍል ፫ እና ፰ ውስጥ ሽማግሌዎችን አስመልክቶ የወጣው መመሪያ በዲያቆናትም ላይ ተግባራዊ ይሆናል።

**አንቀጽ ፲ የሽማግሌዎች ጉባዔ ስብሰባ**

**አንቀጽ ፲ ክፍል ፩ የስብሰባ ቦታና በስልክ አማካይነት የሚደረግ ስብሰባ**

ወርሃዊ ስብሰባ የሽማግሌዎች ጉባዔ በወሰነው መሠረት በሜሪላንድ ከተማና ባካባቢው ወይም በማንኛውም አመቺ ሥፍራ ሊደረግ ይችላል። ቀደም ሲል የተዘጋጀ ቦታ ካልኖረ ስብሰባው በመጋቢው ቢሮ ውስጥ ይካሄዳል።

ልዩ የሽማግሌዎች ስብሰባ ቢያስፈልግ አመቺ ሆኖ እንደተገኘ በሜሪላንድ ከተማና ባካባቢው ወይም ከዚህ ክልል ውጭ ወይም በመጋቢው ቢሮ ውስጥ ይደረጋል።

**ክፍል ፪ ዓመታዊ ስብሰባ**

የሽማግሌዎች ጉባዔ ቤተ ክርስቲያኒቱን በሚመለከት ማለትም ምርጫ ለማድረግ፣ ሥራ ለማረካከብና የድርጅቱን እንቅስቃሴ ለመገምገም በዓመት አንድ ጊዜ ይሰበሰባል።

**ክፍል ፫ ሌሎች ስብሰባዎች**

የሽማግሌዎች ጉባዔ እንደ አስፈላጊነቱ ወይም እንደ ጉዳዮቹ አጣዳፊነት በማንኛውም ወቅት ስብሰባ ሊያካሄድ ይችላል።

**ክፍል ፬ ልዩ ስብሰባ**

ሀ. ስብሰባ የመጥራት ሥልጣን፡

መጋቢው ወይም ምክትል መጋቢው፣ የቤተ ክርስቲያኒቱ ፀሐፊ ወይም የሽማግሌዎች ጉባኤ አባሎች ልዩ ስብሰባ እንዲጠራ ማድረግ ይችላሉ። ሆኖም በቅድሚያ ስብሰባው የሚያስፈልግበትን ምክንያት ለሽማግሌዎች አቅርበው አስፈላጊነቱ የታመነበት መሆን ይኖርበታል።

**ለ. ፩ ማስታወቂያ ወይም ማሳሰቢያ**

የማስታወቂያ አወጣጥ ሁኔታ

እያንዳንዱ የጉባዔ አባል የስብሰባውን ጊዜና ቦታ በሚከተለው ሁኔታ እንዲያውቅ ይደረጋል።

ሀ. በእጅ በሚሰጥ ደብዳቤ።

ለ. በአንደኛ ደረጃ የፖስታ አገልግሎት

ሐ. በስልክና ግለሰቡ ካልተገኘ መልዕክቱን ሊያደርስ ለሚችል ሰው በመንገር።

**ለ. ፪ ማስታወቂያውን ለማዳረስ የሚፈጀው ጊዜ**

በአንደኛ ደረጃ የፖስታ አገልግሎት የሚላከው ማስታወቂያ ስብሰባው ሊደረግ ከታሰበበት ከአራት ቀን በፊት ይኖርበታል። በቴሌፎን፣ በቴሌግራምና በእጅ የሚተላለፉ ማስታወቂያዎች ስብሰባው ከሚደረግበት ቀን ከአርባ ስምንት ሰዓት በፊት ለጉባዔው አባሎች እንዲደርሱ ይደረጋል።

**ለ. ፫ የማስታወቂያ ይዘት**

ማስታወቂያው የስብሰባውን ቦታና ጊዜ በዝርዝር ይገልፃል፣ ይሁን እንጂ ስብሰባው በመጋቢው ቢሮ የሚካሄድ ከሆነ የስብሰባውን ይዘትና ቦታ መጥቀስ አስፈላጊ አይደለም።

**ሐ. ፬ ምልዓተ ጉባዔ**

የሽማግሌዎች ቁጥር ከግማሽ በላይ ሆኖ ሲገኝ ስብሰባው ይካሄዳል። የተሰበሰቡት አባላት ቁጥር ከግማሽ በታች ከሆነ ጉባዔው በሊቀመንበሩ ይበተናል።

**አንቀጽ ፲፩ ሌሎች መጋቢዎችና አገልጋዮች**

፲፩.፩ የቤተ ክርስቲያኒቱ የዕድገት ደረጃ በሚፈቅደው መሠረት ማለትም እንደ አስፈላጊነቱ የቤተ ክርስቲያኒቱ መጋቢ ሌሎች መጋቢዎችንና አገልጋዮችን በሽማግሌዎች ጉባዔ ስምምነት መሠረት ኮትኩቶ በማሳደግ ክህነታቸው በምዕመኑ እንዲፀድቅ ያቀርባል፣ ምዕመናን ካፀደቁለት በኋላ የክህነት መስጠት ሥነ ሥርዓት አካሂዶ በምዕመናን ጉባዔ ፊት ክህነት ይሰጣል።

፲፩.፪ የእነዚህ መጋቢዎችና አገልጋዮች ሃላፊነትና ተግባር በሽማግሌዎች ጉባዔ ይወሰናል።

፲፩.፫ የእኒዚህ መጋቢዎችና አገልጋዮች ብቃት በሽማግሌዎችና በዋናው መጋቢ ደረጃ ስለሆነ ወዲያውኑ የሽማግሌዎች ጉባዔ አባል ይሆናሉ።

፲፩.፬ እነዚህ አገልጋዮች የሚተዳደሩት ለሽማግሌዎችና ለነባር መጋቢ በወጣው ደንብ መሠረት ነው።

**አንቀጽ ፲፪ አባልነት**

ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መመዘኛ ነጥቦች የሚያሟላ በሜሪላንድ የምትገኘው የአዲስ ኪዳን የክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባል መሆን ይችላል።

- ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደግል አዳኙ አድርጎ የተቀበለ፣
- በሕይወቱ ማለትም በአኗኗሩ ክርስቶስን የሚመሰክር፣
- ይህንን ደንብ አንብቦ በዚህ ደንብ መሠረት ሊተዳደር የፈቀደና
- ይህ ደንብ በሚጠይቀው መሠረት የቤተ ክርስቲያኒቱ አባል የሆነ።

**አንቀጽ ፲፪ ክፍል ፩ አባል የመሆን ሥርዓት**

የአዲስ ኪዳን የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን አባል መሆን የሚፈልግ ግለሰብ የእምነት መግለጫውንና «የሕብረት ቃል ኪዳኑን» ወስዶ በጸሎትና በጥሞና አጥንቶ ከመረመረ በላ ፈቃደኝነቱን በፊርማው በማረጋገጥ «የሕብረት ቃል ኪዳን» መግለጫውን ለሽማግሌዎች ጉባዔ ያቀርባል።

**የሕብረት ቃልኪዳን መግለጫ**

በመንፈስ ቅዱስ እርዳታና ምሪት፡

1. በክርስቲያን ፍቅርና በአንድነት ለመራመድ፣ እርስ በእርስ ለመቻቻልና ለመረዳዳት፣
2. በህብረት ለመጸለይ፣ በጸሎት ለመተሳሰብና እንዲሁም ደስታንና ሃዘንን ለመካፈል፣
3. ጥቃት ለማድረስ ሳይሆን ለሌሎች ለማሰብ፣ ባፋጣኝ ይቅርታ ለማድረግና ለመቀበል፣
4. የቤተ ክርስቲያኒቱን መንፈሳዊና የእምነት ትምህርት ጥራት፣ ሰላም፣ ብልጽግና ዕድገት እንዲሁም የመንፈሳዊ እውቀት ብቃትዋን ለመጠበቅ፣
5. ጌታ ባስቻለ መጠን ማናቸውንም የቤተ ክርስቲያኒቱን እንቅስቃሴዎች ለመደገፍ፣
6. የጌታን ምሪት ተመርኩዞ ቤተ ክርስቲያኒቱን፣ ለመርዳት፣ ችግረኞችን ለመደገፍ የቃሉ ስርጭት እንቅስቃሴ እንዳይተጓጎል ለመርዳት፣
7. በግሌና በሕብረት ቋሚ ቃሉን ከቤተሰቤ ጋር የማንበብና የፀሎት ጊዜ እንዲኖረኝ ለማድረግ፣
8. ልጆቼን በእግዚአብሔር ፍቅርና ዕውቀት ለመንከባከብ፣
9. በዚህ ዓለም ስኖር በሰዎች ዘንድ ንፁህ፣ በሥራዬ ታማኝና ተመስጋኝ በመሆን እንዲሁም የዓለምን መሻት በመካድ ለመኖርና፣
10. በምሳሌነት፣ በቃሉና በጸሎት ሌሎችን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ለመሳብ ቃል እገባለሁ።

እኔ________________________________

በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ምሪት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ተቀብዬ አድርጌ የኢትዮጵያ ወንጌላዊት እንደግል አዳኜ ቤተክርስቲያንን የእምነት መግለጫና የሕብረት ቃል ኪዳን በጸሎትና በአምልኮቴ፣ በሕብረቴና በጥሞና አጥንቼ ከመረመርኩ በኋላ በምስክርነቴ ከዚች ስምዋ ከላይ ከተጠቀሰው ከኒው ዮርክ ቤተ ክርስቲያን ጋር በፈቃደኝነት ሕብረት መፍጠሬን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ።

የአመልካች ፊርማ__________________

ቀን______________________________

መጋቢ_________________________

ቀን______________________________

እንደ አስፈላጊነቱ ግለሰቡ የቤተ ክርስቲያኒቱን አቋም፣ እምነትናአገልግሎት በበለጠ እንዲረዳ ልዩ ትምህርት ሊሰጠው ይችላል።

ግለሰቡ በሽማግሌዎች ጉባዔ ፊት ቀርቦ የእምነት ምስክርነቱን ሊሰጥ ይችላል።

አዳዲስ አባሎች በሽማግሌዎች ጉባዔ ውሳኔ መሠረት በቋሚ የምዕመናን ስብሰባ ላይ ቀርበው ራሳቸውን ያስተዋውቃሉ።

**አንቀጽ ፲፪ ክፍል ፪**

የመምረጥ መብት

የመምረጥ መብት ያላቸው ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በላይ የሆነ አባላት ብቻ ናቸው።

**አንቀጽ ፲፪ ክፍል ፫**

የአባላት ተግባር

ሀ. በእግዚአብሔር ፈቃድ መሠረት ሙሉና ያለነቀፋ እስክንሆን ድረስ እርስ በእርስ መተሳሰብ፣ እንደ አንድ አካል በመሆን መደጋገፍና፣ በክርስቶስ እውቀት በቅድስናና በመሽካከም መቆም።

ለ-ምድራዊ ኑሮአችን እስኪያበቃ በንፅህና መመላለስና በሕይወት ምስክርነታችን ነፍሳትን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ለመሳብ መጣር። በንግግራችን፣ በፍቅራችን፣ በእምነታችንና በሕይወታችንም ንጽህና መልካም ክርስቲያናዊ አርአያነት ለማሳየት መጣር።

ሐ. በሕብረት መሰብሰባችንን ሳናቋርጥ የእርስ በርስ መንፈሳዊ ግንኙነትና አምልኮ እንዲሁም ቃሉን የማጥናት ጊዜ እንዲኖረን መጣር፣ለመንከባከብ መጣር። በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ ያሉትን የተቀቡ አገልጋዮች ለመንከባከብ መጣር።

መ. አቅም በፈቀደ መጠን በሃብታችንና በንብረታችን ችግረኞችን መርዳት፣ ቃሉ በመሐከላችን የሚያድግበትንና የሚሰራጭበትን መንገድ መደገፍና ባለን እውቀትና ችሎታ ቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ ተግባራዊ ተሳትፎ ማድረግ ይሆናል።

**አንቀጽ ፲፪ ክፍል ፬**

የአባላት ቅጣት

በቤተ ክርስቲያኒቱ አባል ላይ የቅጣት እርምጃ የሚወሰደው

ሀ. አባሉ የቤተ ክርስቲያኒቱን የእምነት መግለጫ ተጻራሪ ሆኖ ሲገኝ፣ ሮሜ.፲፮፥፲፯ 1ተሰ.፫፥፲፬-፲፭ እና 2ዮሐ.፱፥፲፩

ለ. የግለሰቡ ባህሪይ ለኢየሱስ ክርስቶስ ወይም ለቤተ ክርስቲያኒቱ አሳፋሪ ሆኖ ሲገኝና

ሐ. የቤተ ክርስቲያኒቱን ህልውናና ሕብረት ሊያናጋ የሚችል ባህርይ ሲታይበት።

በእግዚአብሔር ቃል መሠረት የቅጣቱ እርምጃ የሚወስደው በሽማግሌዎች ጉባዔ ብቻ ይሆናል። ይህ እርምጃ የሚወሰደው ለማረምና ለማስተካከል እንጂ

ግለሰቡን ለመጉዳት አይደለም። የሽማግሌዎች ጉባዔ ችግሩን ለማቃለል ያላሰለሰ ጥረት ያደርጋል፣ ማቴ፲፰፥፲፮ 2ጢሞ.፪፥፳፬-፳፮ እና 1ቆሮ.፭፥፪።

የተቻለውን ያህል ከፍተኛ ጥረት ተደርጎ ግለሰቡን ማነፅ ካልተቻለ የሽማግሌዎች ጉባዔ የአባልነት ማስወገጃ ደንብን መሠረት በማድረግ ከቤተ ክርስቲያኒቱ አባልነት ይወገዳል። ይህም የምዕመናን ስብሰባ ላይ ይገለፃል።

ይሁን እንጂ መጋቢው እንደ አስፈላጊነቱና እንደ አጣዳፊነቱ የሽማግሌዎችን ጉባዔ ሳይጠራ አስቀድሞ ማንኛውንም አባል መቅጣት ይችላል። ሆኖም የመጨረሻ ውሳኔ የሚወሰደው በሽማግሌዎች ጉባዔ

ነው።

**አንቀጽ ፲፪ ክፍል ፭**

ከአባልነት መወገድ

አባል ከአባልነቱ የሚወገደው

ሀ. በፈቃደኝነት ከአባልነት ለመሰረዝ ሲጠይቅ

ለ.አንድ አባል ሳያስታውቅ ከስድስት ወር በላይ

ሲቀርና በሽማግሌዎች ጉባኤ ሁሌታው ተጥንቶ ውሳኔ ሲሰጥበትና

ሐ.በሽማግሌዎች ጉባኤ የቅጣት እርምጃ ሲወሰድበት ብቻ ነው።

**አንቀጽ ፲፪ ክፍል ፮**

ከአባልነት የተገለለ ግለሰብ እንደገና ለመመለስ ሲያመለክት የሽማግሌዎች ጉባዔ ነገሩን አጥንቶ ከመረመረ በላ ጉዳዩን ተቀባይነት ያለው ሆኖ ሲያገኘው የአባልነት መብቱ እንደገና እንዲመለስለት ያደርጋል።

**አንቀጽ ፲፫**

ምዕመናን

**አንቀጽ ፲፫ ክፍል ፩**

የምዕመናን ስብሰባ

የምዕመናን ዓመታዊ ስብሰባ እንደ አመቺነቱ በአዲስ ዓመት መጀመሪያ ላይ ይደረጋል። በዚህ ስብሰባ ላይ የተለያዩ የአገልግሎት ዘርፎች ሊቀመናብርት በሽማግሌዎች ጉባኤ ጥያቄ መሠረት ዓመታዊ የሥራ ይዞት ሪፖርት ያቀርባሉ።

**፲፫-፩-፪**

በተጨማሪ የምዕመናን ስብሰባ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የሽማግሌዎች ጉባኤ በቂ ማስታወቂያና ቅስቀሳ በማካሄድ ጥሪ ያደርግና ስብሰባው ይካሄዳል።

**፲፫-፩-፫**

በስብሰባው ወቅት መጋቢው በአስተባባሪነት ሲያገለግል ዋና ፀሐፊጡ የስብሰባው ፀሀፊ በመሆን አገልግሎት ይሰጣል።

**፲፫-፩–፬**

ከዚህ በላይ በተዘረዘረው ደንብ መሠረት በስብሰባው ወቅት የምዕመናን ቁጥር ከግማሽ በላይ ሆኖ ከተገኘ ማምኛውንም ዓይነት ውሳኔ ማስተላለፍ ይቻላል።

**አንቀፅ ፲፫ ክፍል ፪**

የምዕመናን ሐላፊነትና ተግባር

**፲፫-፪-፩**

የክህነት ሥርዓት ማለትም የመጋቢዎችን ክህነትና እንዲሁም የሽማግሌዎችን ምርጫ ምዕመናን ያረጋግጣሉ። ይህም ሥርዓት የሚፈፀመውና ሕጋዊነቱም የሚታወቀው ምልአተ ጉባኤ ሲሞላ ብቻ ነው።

**፲፫-፪-፪**

ምዕመናን መጋቢዎችን፣ ሽማግሌዎችንና ሌሎችንም አገልጋዮች በፀሎት፣ በስጦታ፣ ከዚያም አልፎ በፍቅርና በማክበር ይተባበራሉ፣ እንዲሁም በቤተክርስቲያኒቱ መሪዎች የተሰጣቸውን ላፊነት ይወጣሉ።

**፲፫-፪-፫**

ምዕመናን ከሽማግሌዎች ጉባዔ የሚቀርብላቸውን ጉዳይ በትዕግስትና በማስተዋል አጢነው በድምፅ ብልጫ ይወስናሉ።

**፲፫-፪-፬**

የቤተክርስቲያኒቱን ንብረት ለመሸጥ ለመለወጥ በሚደረገው ስምምነት ላይ በድምጽ ብልጫ ውሳኔ ይሰጣሉ።

**አንቀጽ ፲፬**

**አንቀጽ ፲፬ ክፍል ፩**

ሪፖርት

የሽማግሌዎች ጉባዔ ዓመታዊ የቤተክርስቲያኒቱን ሪፖርትና የሂሳብ ሪፖርት ያቀርባል።

1. የሽማግሌዎች ጉባዔ ከጊዜ ወደ ጊዜ እንደአስፈላጊነቱ የቤተክርስቲያኒቱን የሂሳብ ሪፖርት ያቀርባል።

2. የሽማግሌዎች ጉባዔ የቤተክርስቲያኒቱን ዓመታዊ ሪፖርት ያቀርባል።

3. የሽማግሌዎች ጉባዔ የቤተክርስቲያኒቱን አጠቃላይ ሪፖርት ያቀርባል።

4. የሽማግሌዎች ጉባዔ የወደፊቱን የሥራ ዘመን ያጭርና የረጅም ጊዜ እቅድ አውጥቶ ለምዕመናኑ ይገልፃል።

**አንቀጽ ፲፬ ክፍል ፪**

ክፍያ

የቤተክርስቲያኒቱ ሽማግሌዎችና ሌሎች አገልጋዮች ለሚሰጡት አገልግሎት ምንም ዓይነት ክፍያ አያገኙም።

**አንቀጽ ፲፬-ክፍል ፫**

የአገልግሎት ፈቃድ

- በየጊዜው በሽማግሌዎች ጉባዔ ተሻሽሎ የሚወጣውን ሕግና ሥርዓት፣
- በፀሎት መንፈስ ነገሮችን በማጤን፣
- የሽማግሌዎች ጉባዔ የድምጽ ብልጫ ውሳኔን በመከተልና
- የምዕመናኑን የድምፅ ብልጫ ውሳኔን መሠረት በማድረግ
- ቤተክርስቲያኒቱ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ለሚሰብኩ ሕጋዊ ፈቃድ ትሰጣለች።

**አንቀጽ ፲፬ ክፍል ፬**

ክህነት

ቤተክርስቲያኒቱ ከላይ የተጠቀሱትን ነጥቦች መሠረት በማድረግ የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ለሚሰብኩ ሕጋዊ ፈቃድ ትሰጣለች፣ ትክናለች።

**አንቀጽ ፲፭**

ደንቡን የማሻሻል ይዘት

የደንብ መሻሻል

ይህ ደንብ እንዲሻሻል በሽማግሌዎች ጉባዔ ሦስት አራተኛው ድምጽ ሲደግፍ ሊሻሻል ይችላል፣ የተሻሻለው ደንብ የሚፀድቀው ለምዕመኑ ቀርቦ በድምፅ ብልጫ ድጋፍ ሲያገኝ ብቻ ነው።

**ማረጋገጫ**

ይህ ማረጋገጫ ከላይ በዝርዝር የቀረበው ደንብ የአዲስ ኪዳን የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን መተዳደሪያ ደንብ ትክክለኛና እውነተኛ ግልባጭ መሆኑን እናረጋግጣለን። ይህም ደንብ እ.ኤ.አ. ሜይ 30 1992 በቤተክርስቲያኒቱ ሽማግሌዎች ጉባዔ በአንድ ድምፅ ጸድቋል።

ቀን________________________________

መጋቢ______________________________

ፀሐፊ______________________________